# በወንዞቻችን የውሃ መበከልን ለመቀነስ፣ ለአረንጓዴ ጣሪያ ተመላሽ ማግኘት ይፈልጋሉ?

## ስለዚህ ሀብት ይወቁ።

የንብረት ባለቤቶች አረንጓዴ ጣሪያ በዲሲ ውስጥ ባሉ የመኖሪያ ህንጻ፣ የንግድ ህንጻ ወይም የማህበረሰብ ቦታዎች ባሉ ታላሚ አካባቢዎች (ሰማያዊ ምልክት በእዚህ ካርታ) ላይ በመግጠማቸው ተመላሽ ሊያገኙ ይችላሉ። አረንጓዴ ጣሪያዎች የተክል እድገትን ይደግፋል እንዲሁም የዝናብ ውሃን በመያዝ በዝናብ የሚመጣውን ብክለት ይቀንሳል። እኛ —የዲሲ መንግስት— **$15 በስኩዌር ጫማ** (እስከ አረንጓዴ ጣሪያዎ ዋጋ ድረስ) ተመላሽ እናቀርባለን። ለምሳሌ፣ 100 ስኩዌር ጫማ አረንጓዴ ጣራ ከገጠሙ፣ $1,500 ተመላሽ ሊያገኙ ይችላሉ።

እንዲሁም፣ ለትናንሽ የንብረት ባለቤቶች (2,500 ስኩዌር ጫማ ወይም ከዚያ በታች ለሆኑ ህንጻዎች)፣ ስትራክቸራል መሃንዲሱ ገጠማው ደህንነቱን የተጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስፈልገውን የንብረትዎን ምዘና ክፍያ ለመፈጸም እንዲረዳ **እስከ $250** የሚሆን ተመላሽ እናቀርባለን።

ይህ ፕሮግራም RiverSmart Rooftops ይባላል እንዲሁም በኢነርጂ እና አካባቢ ዲፓርትመንት በአካባቢው ካለው Designgreen ከሚባለው ትንሽ ንግድ ጋር በመተባበር ቀርቧል።

## ብቁ መሆንዎን ያረጋግጡ።

እነዚህ መግለጫዎች **በሙሉ** እውነት ከሆኑ እርስዎ ብቁ ነዎት ማለት ነው:

- በዲሲ ውስጥ የመኖሪያ ህንጻ፣ የንግድ ህንጻ፣ የአምልኮ ቤት ወይም የማህበረሰብ ስፍራ ካለዎት።
- ንብረትዎ በዲሲ ማዘጋጃ ቤት የፍሳሽ ማስወገጃ ሲስተም ውስጥ ከሆነ። በዚህ ካርታ ላይ አድራሻዎን ይፈልጉ እና በሰማያዊ የሆነው ህንጻ ላይ ከሆነ፣ ንብረትዎ ለፕሮግራሙ ብቁ ነው።
- ንብረትዎ ቀድሞ የአረንጓዴ ጣሪያ አልተገጠመለትም።
- የአካባቢ ዝናብ ውሃ መቆጣጠሪያ እና የአረንጓዴ አካባቢ ክፍፍል መስፈርቶችን ለማሟላት ህንጻዎ እንደ አረንጓዴ ጣሪያዎች ያሉ የአረንጓዴ ኢንፍራስትራክቸር የሚፈልግ ከሆነ፣ ከእርስዎ የደንብ መስፈርቶች ውጪ አረንጓዴ ጣሪያ ለመግጠም እቅድ ያወጣሉ። እርግጠኛ ባይሆኑም ያመልክቱ ከዛም መስፈርቶቹን እኛ እንመለከታቸዋለን።

ለዚህ ተመላሽ በሁሉም መጠኖች ያሉ ንብረቶች ብቁ ናቸው። የሚያመለክቱበት ንብረት ዲሲ ውስጥ እስከሆነ ድረስ፣ ለማመልከት ዲሲ ውስጥ መኖር አይጠበቅብዎትም።

## ያመልክቱ።

1. አጭር የ RiverSmart Rooftop [የፍላጎት ቅጽን] ስለራስዎ እና ስለንብረትዎ በትንሹ ከሚናገረው ዝርዝሮች ጋር ይሙሉ። ካስገቡ በኋላ፣ የፍላጎት ቅጽዎ እንደገባ የሚያረጋግጥ የራስ ሰር ኢሜይል ይቀበላሉ።
2. በአንድ የስራ ቀን ውስጥ፣ እርስዎ ብቁ ሊሆኑ የሚችሉ ከሆኑ ለማሳወቅ የእኛ አጋር የሆነው Designgreen ያነጋግርዎታል። Designgreen የእርስዎን ብቁነት ለማረጋገጥ ጥቂት ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ሊጠይቁዎት ይችላሉ።
3. Designgreen በማመልከቻው ሂደት እና በእያንዳንዱ ደረጃ ላይ ስለሚያስፈልጉ ሰነዶች አብረዎት ይራመዳሉ። ይህ ሂደት ብዙውን ጊዜ ከ 3-6 ወራትን ሲፈጅ የሚያጠቃልለውም፡
    - የጣሪያውን የአሁን ሁኔታ ፎቶዎችን ማንሳትና ማስገባት።
    - የሚገጠመውን ክብደት መሸከም እንደሚችል ለማረጋገጥ የስትራክቸራል መሃንዲሱ ምዘና እንዲሰጥ ማድረግ።
    - አረንጓዴ ጣሪያ ለመግጠም የወጪውን ግምት ማግኘት።
    - ስራውን እንዲሰሩ ስራ ተቋራጭና ንድፍ አውጪ መምረጥ።
    - የኢንዱስትሪ ደረጃዎችን እንዲያሟሉ የአረንጓዴ ጣሪያዎችን ንድፍ ማስወጣት።
    - ከ DOEE ተመላሽ ፈቃድ ውጪ ያሉ የዝርጋታ ወጪዎችን ለመሸፈን ገንዘብን መለየት።
    - የአረንጓዴ ጣሪያን ለሁለት አመት ለመጠበቅ የእቅድ ስዕሎቹን ማስገባት፣ ከሸማች እና ተቆጣጣሪ ጉዳዮች ዲፓርትመንት ዲፓርትመንት (DCRA) ፈቃድ፣ ከስራ ተቋራጭዎ ዋስትና እንዲሁም ከስራ ተቋራጭዎ ጋር ስምምነት ያስፈልጋል።
4. ከላይ ያሉትን ሁሉንም ደረጃዎች ካጠናቀቁ በኋላ፣ የአረንጓዴ ጣሪያ መግጠም ለመቀጠል በመስማማት እና ተመላሹን በመቀበል ውሉን ይፈርማሉ።

በማንኛውም ሰዓት ማመልከት ይችላሉ። ብቁ ካልሆኑ፣ Designgreen በኢሜይል ያሳውቅዎታል። ሁኔታዎ ከተቀየረ ዳግም ማመልከት ይችላሉ።

## ተጨማሪ መረጃ ይሰብስቡ።

## ካመለከትኩ በኋላ ምን ይሆናል?

1. ውሉን ከፈረሙ በኋላ Designgreen የእርስዎን ተመላሽ 10% ያህል ቼክ ይልክልዎታል።
2. የአረንጓዴ ጣሪያ ገጠማውን ይቀጥላሉ።
3. ገጠማው እንደተጠናቀቀ ለማረጋገጥ፣ እርስዎ የአረንጓዴ ጣሪያ ፎቶዎች እና የስራ ተቋራጩ ለ Designgreen የሰጠውን ደረሰኝ ያስገባሉ።
4. Designgreen ገጠማው መጠናቀቁን እና ሁሉንም መስፈርቶች ማሟላቱን ካረጋገጠ በኋላ፣ የእርስዎን ቀሪ 90% ተመላሽ ይሰጥዎታል።

5. በእኛ የጥገና [ቼክሊስት](#) እና [ዝርዝር በራሪ ጽሑፍ](#) ላይ ያለውን በመከተል አረንጓዴ ጣሪያዎን ይመለከታሉ፣ ውሃ ያደርጉበታል እንዲሁም አላስፈላጊ ነገሮችን ያስወግዳሉ። የእርስዎ አረንጓዴ ጣሪያዎች ጤናማና በትክክል እየሰሩ እንደሆነ ለማረጋገጥ መደበኛ ክትትል ያስፈልጋቸዋል።

የአረንጓዴ ጣሪያ ገጠማዎን ካልጨረሱ፣ የመጀመሪያ 10% ክፍያን ለ Designgreen መመለስ ይኖርብዎታል። ዝርጋታውን ለመጨረስ መጀመሪያ ከታቀደው ጊዜ የበለጠ የሚፈልጉ ከሆነ፣ Designgreen ጭማሪውን ጊዜ ሊሰጥዎት ይችላል።

## ሁሉም ብቁ አመልካቾች ተመላሽ ያገኛሉ?

ተመላሾች መጀመሪያ በመጣ፣ መጀመሪያ በተስተናገደ መሰረት ላይ ቀርበዋል።

## ማወቅ ያለብኝ ተጨማሪ መስፈርቶች አሉ?

በቅርቡ በተጠናቀቁ ወይም አሁን ባሉ አረንጓዴ ጣሪያዎች ላይ ያሉ ማመልከቻዎች ተቀባይነት የላቸውም። ለአረንጓዴ ጣሪያ ፈቃድ ከማግኘትዎ በፊት፣ ለተመላሹ ማመልከት አለብዎት።

## ጥያቄዎች ቢኖሩኝ ማነጋገር ያለብኝ ማንን ነው?

መጀመሪያ፣ ከገጹ ታች ቦታ ላይ የሚገኘውን በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎችን ይመልከቱ። አሁንም ድረስ ጥያቄዎች ካሉዎት፣ ከሰኞ እስከ አርብ ከ 9am እስከ 5pm በ (202) 849-0388 ላይ Designgreen እባክዎ ያግኙ። ወይም፣ ለ Rebecca Stack በ rcstack@designgreenllc.com ላይ በርዕሰ መስመር “Green Roof Question” ተጠቅመው ኢሜይል ሊያደርጉላት ይችላሉ።

## ቤቴን የበለጠ ለአካባቢ ተስማሚ ለማድረግ አሁንም ቢሆን እርዳታ ያስፈልገኛል። ምን ማድረግ አለብኝ?

የእርስዎን ቤት የበለጠ [ለአካባቢ ተስማሚ](#) ለማድረግ የሚረዱ ሌሎች ሐብቶችን መረጃ ማግኘት ይችላሉ።

# በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

## አረንጓዴ ጣሪያ ምንድን ነው?

አረንጓዴ ጣሪያዎች የሚሰሩት የዝናብ ውሃን ለመያዝ እና ለመቆጣጠር እንዲረዳ፣ የሚያድግ ሚዲያ እና ተክሎችን በጣሪያዎ ላይ በማድረግ ነው። ይህ በዲሲ የውሃ ማስተላለፊያዎች ላይ የዝናብ ውሃን እና ብክለትን ለመቀነስ ይረዳል። በህንጻዎ አካባቢ ያለውን የአየር ጥራት እንዲሁ ለማሻሻል ይረዳል እንዲሁም የህንጻዎን የሃይል ውጤታማነትንም ይጨምራል።

## አረንጓዴ ጣሪያዎች ጥገና ይፈልጋሉ?

ልክ እንደሌሎች አረንጓዴ የመሰረተ ልማተ ዓይነቶች፣ አረንጓዴ ጣሪያዎች ጤናማ እና በትክክል እየሰሩ እንደሆነ ለማረጋገጥ መደበኛ ጥገና ይፈልጋሉ። [የአረንጓዴ ጣሪያዎን እንዴት እንደሚጠብቁ](#) ይማሩ።

## አረንጓዴ ጣሪያ መግጠም እፈልጋለሁ፣ ነገር ግን የሚያስፈልገው የመዋቅር ምዘና ውድ ነው። ምን ማድረግ እችላለሁ?

ህንጻዎ 2,500 ስኩዌር ጫማና ከዚያ በታች ከሆነ፣ የስትራክቸራል መሃንዲሱ ንብረትዎን ለሚመዝንበት ክፍያ ለመርዳት እስከ $250 ተመላሽ ልናቀርብ እንችላለን።

## አረንጓዴ ጣሪያ መግጠም እፈልጋለሁ ነገር ግን የእኔ ጣሪያ ክብደቱን ለመሸከም ጠንካራ አይደለም። ምን ማድረግ እችላለሁ?

አሁን ባለው ጣሪያ ላይ አረንጓዴ ጣሪያ የሚገጥሙ ከሆነ፣ የእርስዎ ስትራክቸራል መሃንዲስ ጣሪያዎ የአረንጓዴ ጣሪያን ክብደት ለመሸከም ጠንካራ እንዳልሆነ ሊነግርዎት ይችላል። በሚያሳዝን ሁኔታ፣ አሁን ያለውን ጣሪያ በተጨማሪ ለመዋቅር ድጋፍ ማጠናከር የሚወጣውን ክፍያዎች ተመላሹ አይሸፍንም።

## አረንጓዴ ጣሪያ በመትከል የሚገኙ ሌሎች ማንኛውም የገንዘብ ጥቅማ ጥቅሞች አሉ?

አዎ! ለዚህ ፕሮግራም ሲያመለክቱ፣ በ DC Water ክፍያዎ ላይ RiverSmart Rewards ለሚባለው ቅናሽ ማመልከት እንዲችሉ እንረዳዎታለን። እንደ አረንጓዴ ጣሪያዎች የመሰሉ አረንጓዴ ኢንፍራስትራክቸር ጋር ያሉ ንብረቶቻቸውን ከዝናብ ውሃ ለሚከላከሉ የንብረት ባለቤቶች የተደረገ ቅናሽ ነው።

## ለሌላ አይነት የአረንጓዴ ኢንፍራስትራክቸር ለመግጠምና ለመክፈል እርዳታ ማግኘት እችላለሁ?

አዎ! የእኛ RiverSmart Homes ፕሮግራም ለዝናብ በርሜሎች፣ የዝናብ አትክልት ስፍራዎች፣ አስተላላፊ ንጣፍ እንዲሁም ሌላም ያሉ የአረንጓዴ ፕሮጀክቶች ዝርጋታ የቴክኒክ እና የገንዘብ ድጋፍ እናደርጋለን። ነጠላ የቤተሰብ ቤት (ወይም አራት ወይም ከዛ በታች ክፍሎች ያሉት ህንጻ) ካለዎት፣ ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።

ማንኛውም አይነት የመኖሪያ ህንጻ፣ የንግድ ህንጻ ወይም የማህበረሰፍ ስፍራ ያሏቸው የንብረት ባለቤቶች፣ እኛ —የዲሲ መንግስት— እንዲሁ ለአስተላላፊ ንጣፎች፣ የዝናብ አትክልት ስፍራዎች፣ የዝናብ በርሜሎች፣ እንዲሁም ለዛፍ መትከሎች ተመላሾችን እናቀርባለን። የብቁነት መስፈርት፣ የማመልከቻ ሂደት፣ እንዲሁም የተመላሽ መጠን በፕሮጀክቱ አይነት ላይ በመመስረት ይለያያል እንዲሁም ከመገንባትዎ በፊት መተግበር ሊኖርብዎት ይችላል። የእኛ ፕሮግራሞች ከ RiverSmart Homes በተለየ፣ የመጠባበቂያ ዝርዝር የላቸውም።

## ተቀባይነት ሳላገኝ ብቀር ለፕሮግራሙ እንደገና ማመልከት እችላለሁ?

አዎ። የሁኔታዎ መቀየር ብቁ ያደርገኛል ብለው ካሰቡ፣ ለ RiverSmart Rooftops ዳግም ማመልከት ይችላሉ። ለቀድሞ ማመልከቻዎ የመከታተያ ቁጥር ካለዎት፣ ዳግም ሲያመለክቱ እባክዎ ቁጥሩን ያቅርቡ።

## አረንጓዴ ኢንፍራስትራክቸር የዲሲ ከተማን እንዴት ሊረዳ ይችላል?

አረንጓዴ ኢንፍራስትራክቸር የዝናብ ውሃ ፍሰት እንዲቀንስ ሲረዳ ይህም የ Anacostia ወንዝን፣ Potomac ወንዝን እንዲሁም Rock Creek ከአደገኛ መበከል ለመጠበቅ ይረዳል።

*ይህ ገጽ ለመጨረሻ ጊዜ የተሻሻለው ሜይ 2021 ነው።*